የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/705

ቀን መስከረም 2 ቀን 2015 ዓ.ም.

**ለብልጽግና ፓርቲ (ብልፅግና)**

**አዲስ አበባ**

ፓርቲያችሁ መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ብፓ/ምፕዋፅን/1062/14 በተፃፈ ደብዳቤ ከመጋቢት 2- 4 / 2014 ዓ.ም. የተደረገውን የፓርቲው 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሚመለከት የጉባኤውን ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረቡ ይታወሳል።

ቦርዱ ሚያዝያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ያቀረባቸውን የጠቅላላ ጉባኤ ሰነዶች እና ጠቅላላ ጉባኤውን በታዘቡት የቦርዱ ተወካዮች የቀረበውን ሪፖርት መርምሮ የጠቅላላ ጉባኤውን ሂደት፣ በጉባኤው የተላለፉ ውሳኔዎች እና የተደረጉ ምርጫዎችን በተመለከተ ውሣኔ ለመስጠት ተጨማሪ ሰነዶች እና መረጃዎችን ማየት ያስፈልጋል ሲል በመወሰኑ ፓርቲው ሰነዶቹን እንዲያቀርብ ሚያዝያ 19 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አ1162/11/592 እና ሐምሌ 7 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አ1162/11/664 በተፃፉ ደብዳቤዎች ተገልጾለታል።

በዚሁ መሠረት ፓርቲው ሚያዝያ 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ብፓ/ምፕዋጽን/1194/14 እና ሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ብፓ/ም/ፕ/ዋና/ጽ/1609/14 በተፃፉ ደብዳቤዎች ተጨማሪ ሰነዶች ለቦርዱ አቅርቧል።

ቦርዱ ነሐሴ 20 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን ሰነዶች ከሕጉ፣ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የቦርዱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት አንፃር መርምሮ ከዚህ የሚከተለውን ውሣኔ አሳልፏል።

**I. ፓርቲው ያካሄዳቸውን ምርጫዎች በተመለከተ**

ሀ/ ቦርዱ ጉዳዩን እንደመረመረው ፓርቲው ያቀረበው በጉባዔው የተመረጡ ***የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ዝርዝር*** የቦርዱ ታዛቢዎች በወቅቱ የምርጫው ውጤት ሲገለፅ መዝግበው ካቀረቡት ዝርዝር ጋር ልዩነት ያለው በመሆኑ

ለድምጽዎ የሚያምኑን



ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ - ገጽ www.nebe.org.et

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ +251 115 153468

ፋክስ +251 115 510025

ፓርቲው ተጨማሪ ማብራሪያ አቅርቧል። በዚህም መሰረት በፓርቲው ጉባኤ የተመረጡት የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ስብጥር በመተዳደሪያ ደንቡ ከተመለከተው የተመጣጣኝ ውክልና መርህ ጋር የሚስማማ ሆኖ ባለመገኘቱ ማዕከላዊ ኮሚቴው ከጉባኤው ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት  የተመረጡ አስር አባላት በውድድሩ ተሳትፈው አነስተኛ ድምፅ ባላቸው ሌሎች አባላት እንዲተኩ መወሰኑ ተገልጿል። ይህም የተፈፀመው በጠቅላላ ጉባኤው ላይ በተደረገ ስምምነት ስለመሆኑ ለማሳየትም ፓርቲው አረጋግጦ ባቀረበው የጉባዔው  ቃለ ጉባኤ ይህ ጉዳይ ስምምነት  የተደረሰበት ነጥብ እንደሆነ ተመዝግቦ ቀርቧል። ይሁንእና ሶስት አባላት የነበሩት የቦርዱ ታዛቢዎች ቡድን ባቀረቡት ሪፖርት ይህ ጉዳይ በጉባዔው ላይ ለውይይት እንዳልቀረበ ለቦርዱ አረጋግጧል።

በመሆኑም  በህጉ እና በፓርቲው መተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በፓርቲው የመጨረሻ ውሳኔ  ሰጪ አካል በሆነው የጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡት ዝርዝራቸው ከዚህ ደብዳቤ ጋር የተያያዘው  የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ብቻ በመሆናቸው፥ እነዚህ የቦርዱ ታዛቢዎች በተገኙበት እና ምርጫቸውን ያረጋገጡትን  የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ተቀብሎ መዝግቦ ፓርቲው በዚሁ መሰረት እንዲፈፅም ወስኗል።

ለ/ **የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላትን በተመለከተ፡** ተመርጠዋል ተብለው የቀረቡት የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላት በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 74/3 ግልጽ፤ ነጻና ፍትሃዊ በሆነ በሚስጥር በሚሰጥ ድምጽ ያልተመረጡ  እንዲሁም በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 23/1 መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ ሰጥቶ የመረጣቸው ሳይሆን ለጠቅላላ ጉባዔው ስም ዝርዝራቸው ለጉባዔው የተገለፀ መሆኑ  ጠቅላላ ጉባኤውን በታዘቡት የቦርዱ ታዛቢዎች ተረጋግጧል።

በመሆኑም ፓርቲው ይህ ውሳኔ ከተገለጸበት ከመስከረም  2 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በ4ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ጥር 2 ቀን 2015 ዓ.ም. ድረስ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላት ምርጫ እንዲያደርግ ቦርዱ ወስኗል።

ሐ/ የማዕከላዊ ኮሚቴው ጉባዔው በተደረገበት ወቅት በስፍራው ባደረገው ***የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምርጫ*** ስብሰባ ላይ የቦርዱ ታዛቢዎች ስብሰባው ላይ እንዲገኙ ሳይፈቀድላቸው ቀርቷል። ቦርዱ ሌሎች ፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባኤ በሚያደርጉበት ቀን በሚያካሄዱት የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ የቦርዱ ታዛቢዎች የመገኘት በጎ ልምምድ አለ። ይሁንና ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤውን ባደረገበት ቀን በተካሄደው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ ላይ የቦርዱ ታዛቢዎች አለመገኘታቸው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት አመራረጥን እንዳይታዘቡ አድርጓል። ለወደፊት ተመሳሳይ ክልከላ እንዳይደረግ ቦርዱ ወስኗል።

## II. በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ማስተካከያ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በሚመለከት

1. በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17/1ቀ/ የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ እንዳለ ቢገልጽም የኮሚቴውን ሚና፤ አባላቱ የሚመረጡበት ሂደት እና የስራ ሃላፊነታቸውን የሚገልጽ ድንጋጌ በደንቡ ያልተካተተ በመሆኑ ፓርቲው ወደፊት በሚያደርገው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎበት እንዲቀርብ፤

2. የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላት ብዛት፣ ስጥብርና አመራረጥን በተመለከተ ግልፅ የሆነ መመሪያ ፓርቲው የሌለው መሆኑን ቦርዱ ከቀረበለት የታዛቢዎች ሪፖርት የተገነዘበ በመሆኑ፤ ይህ መመሪያ በሚመለከተው የፓርቲው አካል እንዲወጣ ፤

3. የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 7/4ሸ/ ከፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ 50%+1 እና ከዚያ በላይ ከተሟላ ምልዓተ ጉባኤ እንደተሟላ የሚደነግግ ሲሆን በአንቀፅ 16(4) መሰረት ደግሞ የጉባኤ ተሳታፊ ብዛት ከ500 በላይ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፤ ሆኖም ከአዋጁ አንቀፅ 74/1ሰ/ አንፃር ሲታይ ዝቅተኛው የአገር አቀፍ ፓርቲ የጉባኤ ቁጥር 500 መሆን አለበት ከሚለው አስገዳጅ ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ ፓርቲው ወደፊት በሚያደርገው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎበት እንዲቀርብ፤

4. በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74/1ሐ/ መሰረት የፓርቲየምርጫ ሥርዓት በግልጽ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ሊካተት የሚገባው ጉዳይ በመሆኑ በዝርዝር በፓርቲው ጉባኤ ላይ የሚከናወን ምርጫ የምርጫ አስፈጻሚ የሆነው አካል ማን እንደሆነ ፤ ይህ አካል እንዴት እንደሚመረጥ፤ የምርጫው አካሄድ ምን እንደሚመስል (ለምሳሌ፡- የዕጩ ጥቆማ፤ በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ፤ ድምጽ ቆጠራ፤ ውጤት ማዳመር፤ ውጤት አገላለጽ እና ውጤት ማጽደቅ) የሚሉትና ሌሎች የምርጫ ሂደቶች በግልጽ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ያልተካተተ በመሆኑ ስብሰባ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎበት እንዲቀርብ በቀጣዩ የፓርቲው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲፀድቅ፤

5. በጠቅላላ ጉባኤው ላይ የፓርቲው ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንት አመራረጥን በተመለከተ እጩ የሆነ ሰው አስመራጭ የሚሆን ከሆነ በተለይም ይህ አስመራጭ የሀገር መሪ ኃላፊነት ላይ የተቀመጠ ሲሆን በምርጫው አካሄድ ላይ ተፅእኖ የሚያመጣ መሆኑ ግልፅ በመሆኑ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የምርጫ አካሄዱን አስመልክቶ የሚመረጥ ወይም ዕጩ ሆኖ የሚቀርብ ሰው አስመራጭ እንዳይሆን የሚከለክል አንቀፅ በማስፈር መተዳደሪያ ደንቡ አስተካክሎ ፓርቲው በሚያደርገው ቀጣይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲፀድቅ፤

6. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 18/8/ሠ መሠረት ፓርቲውን ወክለው በምርጫ የሚሳተፉ አባላትን ስለሚመረጡበት ሁኔታ ማዕከላዊ ኮሚቴው መመሪያ እንደሚያወጣ በተገለፀው መሠረት በአዋጁ አንቀፅ 74/1/ቸ መሠረት መመሪያው ወጥቶ ለቦርዱ እንዲቀርብ ተወስኗል፡፡

## *III. የመተባበር ግዴታን በተመለከተ*

በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 161 እንደተደነገገው ቦርዱ በዚህ ህግ የተሰጡትን ሀላፊነቶችን ለመወጣት ያስፈልጋል ያላቸውን ተግባራት ስራ ላይ ለማዋል ይህን ፓርቲ ጨምሮ ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ (Duty to Cooperate) እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ ፓርቲዎች በሚያደርጓቸው ጉባዔዎች ሂደቱ በህግ እና በመተዳደሪያ ደንብ

መሰረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ቦርዱ በሚሰራው የትዝብት ስራ ጋር በተያያዘ ባለሙያዎች በፅሁፍ ከሚይዙት ዘገባ በተጨማሪ ክንውኑ በቦርዱ ባለሙያዎች በቪዲዮ እንዲቀረፅ የአሰራር መመሪያ ሰጥቶ አብዛኞቹ ፓርቲዎች በዚህ አግባብ ፈፅመዋል።

ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ከመጋቢት 2 - 4/2014 ዓ.ም. በቦርዱ የተመደቡ ባለሙያዎች ሂደቱን ለመቅረጽ ተከልክለዋል።

ፓርቲው ይህ ተቀባይነት የሌለው ተግባር እንዳይደገም ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ቦርዱ ወስኗል።

በመሆኑም ፓርቲው ከላይ በተገለፀው መሠረት ማስተካከያ እንዲያደርግባቸው ከተገለፁት ነጥቦች ውጭ ያሉት ፓርቲው ከመጋቢት 2-4/2014 ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ያሳለፋቸውን ውሣኔዎች ቦርዱ የመዘገበ መሆኑን እንገልፃለን።

ከበጎ ምኞት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ